# የተለመዱ/የጥሩ ልምዶች ማረጋገጫ ዝርዝሮች

የንድፍ ባለሙያዎች የኤፍ/ኤች/ኤ እና የኤ/ዲ/ኤ የተደራሽነት መስፈርቶችን የመከተል ግዴታ አለባቸው። ቀጥሎ እነዚህን መስፈርቶች እንደጠበቁ እንዲቆዩ ሊያግዙዎት የሚችሉ አንዳንድ ምርጥ ልምዶች ቀርበዋል፥

- የፍትሃዊ መኖሪያ ቤቶች ድንጋጌ የንድፍ መመሪያ ሰነድን በተለይም ምዕራፍ 2፥ ተደራሽ የሆነ እና ጥቅም ላይ የሚውል የሕዝብ እና የጋራ መገልገያ ቦታዎች የሚለውን ክፍል በተደጋጋሚነት ማጣቀስ።
- ለቀጣይ የትምህርት ዩኒቶችዎ (CEUs-ሲ/ኢ/ዩ) ተደራሽነትን የሚያጎሉ ኮርሶችን ይምረጡ።
- የሚፈለገውን ግልስ የወለል ቦታ፣ በቂ የሆነ ቁሳቁሶችን መከላከያዎችን፣ እና ወደ ሁሉም የወለሎች ፕላኖች እና ንድፎች መዳረሻ መስመሮችን ያዘጋጁ።
- ለዕቅድዎ እንደ መጨረሻ የማነጻጸሪያ ዝርዝር የሚያለግል የሁሉንም የተደራሽነት መስፈርቶች የያዘ የማረጋገጫ ዝርዝር ያዘጋጁ።
- የ 3ኛ ወገን የተደራሽነት ባለሙያዎች እና/ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች የሰሩትን ንድፍ እንዲገመግሙት ያድርጉ።

*Advancing Civil Rights*
*For Over a Quarter Century*

የእኩልነት መብቶች ማእከል (ERC-ኢ/አር/ሲ) በሚገኝበት ማህበረሰብ በግሬተር ዋሽንግተን፣ ዲሲ እና በመላ ሃገሪቱ ውስጥ በመኖሪያ ቤት፣ በስራ ቅጥር፣ በሕዝባሚ መኖሪያዎች ዙሪያ ሕገ-ወጥ የሆኑ እና ፍትሃዊ ያልሆኑ አድሏዊነቶችን ለመለየት እና ለማስወገድ የሚሞክር የሰብዓዊ መብቶች ድርጅት ነው።

## የእኩልነት መብቶች ማእከል

**Main - 202.234.3062**
**Toll Free - 866.549.0009**
**Relay 711**

www.equalrightscenter.org
info@equalrightscenter.org

©የእኩልነት መብቶች ማእከል 2017

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው!

*የዚህን ህትመት መሰረት ያቀረበው ስራ በአሜሪካ የመኖሪያ ቤቶች እና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት በቀረበ የገንዘብ እርዳታ ተደግፏል።የሥራው ፍሬ ነገሮች እና ውጤቶች ለህዝብ አገልግሎት የቀረቡ ናቸው። በዚህ ህትመት ውስጥ ለቀረቡ ጽሁፎች እና ለሚሰጡት ትርጓሜዎች ትክክለኛነት ደራሲው እና አታሚው ሙሉ ኃላፊነት አላቸው። እነዚህ ትርጓሜዎች የግድ የፌዴራል መንግስትን አመለካከት ያንፀባርቃሉ ማለት አይደለም።*

# የውስጥ ንድፍ እና ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤቶች ድንጋጌ

*Advancing Civil Rights*
*For Over a Quarter Century*



www.equalrightscenter.org

# ያውቁ ነበር?


ፍትሃዊ የመኖሪያ ቤቶች ድንጋጌ (FHA-ኤፍ/ኤች/ኤ) ንድፍ እና ግንባታ መስፈርቶች ለሁሉም የህዝብ የመገልገያ ስፍራዎች ተግባራዊ ይሆናሉ። የህዝብ የመገልገያ ስፍራዎች ማለት፥ ክፍሎች፣ ቦታዎች፣ እና በባለብዙ ቤተሰብ የመኖሪያ ህንጻዎች ውስጥ እና ውጭ የሚገኙ ለሁሉም ነዋሪዎች እና የነዋሪዎች እንግዶች እንዲያገለግሉ የተሰሩ ቦታዎች ናቸው።

የህዝብ የመገልገያ ስፍራዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፥

- የአካል ብቃት/የስፖርት ማእከሎች
- የባርባኪው ቦታዎች
- የውሻ ማጫወቻ ቦታዎች/ፓርኮች
- ላውንጆች/የጌም መጫወቻ ክፍሎች
- የፊልም ማሳያዎች/የሜዲያ ክፍሎች
- የገበያ ማእከሎች
- የዋና ገንዳዎች/የመዋኛ ስፍራዎች

የህዝብ የመገልገያ ስፍራዎች የተደራሽነት መስፈርቶች ከአካል ጉዳት ጋር የሚኖሩ አሜሪካኖች ድንጋጌ (ADA-ኤ/ዲ/ኤ) ስር የተካተቱ ናቸው። የህዝብ የመገልገያ ስፍራዎች ለማህበረሰቡ አገልግሎት የተዘጋጁ ማንኛውም የህንጻ ውስጣዊ ወይም ውጫዊ ክፍሎች ሲሆኑ የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፥

- የሚከራዩ ቢሮዎች/ሊዚንግ ኦፊስስ
- ሞዴል ክፍሎች/ ሞዴል ዩኒትስ



የዲዛይን/የንድፍ ባለሙያዎች በባለብዙ ቤተሰብ መኖሪያዎች ውስጥ የቦታዎችን ንድፍ በሚያዘጋጁበት ወቅት በኤፍ/ኤች/ኤ እና በኤ/ዲ/ኤ ስር ያሉ የተደራሽነት መስፈርቶችን ማጣመር አለባቸው። ይህን ሳያደርጉ መቅረት በእነዚህ ሕጎች ስር ያሉ የተደራሽነት ግዴታዎቻቸውን ባለማሟላት በንድፍ ድርጅቶች ወይም የንድፍ ባለሙያዎች ላይ ክስ እንዲመሰረት ሊያደርግ ይችላል።

## ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ዋና ዋና ነገሮች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፥




የጥበብ ስራዎች፣ የመብራት እና ተያያዥ እቃዎች፣ በግድግዳ ላይ የሚሰቀሉ ቴሌቪዥኖች እና የመሬት አቀማመጦች በትክክል ካልተሰሩ/ካልተገጠሙ ማየት ለተሳናቸው ወይም ዝቅተኛ የሆነ እይታ ላላቸው ነዋሪዎች አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ከ27" ዝቅ ብሎ በግልጽ የተቀመጠ መከላከያ ከሌለ በቀር፣ አካላት/ነገሮች ከ 4" የበለጠ ከግድግዳው አልፈው መውጣት ወይም ወደ መንቀሳቀሻ ክልል አልፈው መሰራት የለባቸውም።



አንድ አገልግሎት፣ አቅርቦት፣ ወይም ቦታ ለነዋሪዎች የጋራ መገልገያነት በሚዘጋጅበት ወቅት ሁሉ፣ ዊልቼር ለሚጠቀሙ ሰዎች ተደራሽ ሆኖ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን ተደራሽነት ባለው ቦታ መሆን ይኖርበታል (ከፍታው፣ እና ቢያንስ 36" ያህል ስፋት)። በርካታ አገልግሎት መስጫዎች የሚቀርቡ ከሆነ፣ እነዚህ አገልግሎቶች በበቂ ሁኔታ መኖር ወይም ተደራሽ መሆን አለባቸው።

## ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ የተለመዱ ስህተቶች፥



- ባር እና የመሳሰሉት ላይ የሚገኙ በቁመታቸው ከፍ ያሉ ጠረጴዛዎች ወይም ካውንተሮች ያሏቸው ላውንጆች ወይም ቦታዎች ውስጥ ከፍታው ከ 36" በላይ ያልሆነ እና ቢያንስ 36" ስፋት ላለው ክፍል ተደራሽነት የሌላቸው ከሆነ።
- እያንዳንዱ የአካል ብቃት መሣሪያዎች ወይም ቴሌቪዥኖች እና የዲቪዲ ማጫወቻዎች የመሳሰሉት በአንድ ቦታ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ ነገሮች እና አገልግሎቶች ዊልቼር ለሚጠቀሙ ሰዎች በፊትለፊት ወይም በጎን ቀርቦ ለመገልገል የሚያስችል በቂ የሆነ (30"x 48") የወለል ቦታ የሌላቸው ከሆነ።
- እንደ ባርባኪው የመሳሰሉት የህብረት መዝናኛ/መገልገያ ነገሮች የመቆጣጠሪያ ወይም የመስሪያ ክፍሎቻቸው ተደራሽነት ባለው ሁኔታዎች ላይ የማይገኙ ከሆነ (ከ 48" ከፍታ በታች፣ ያልተሸፈኑ)።
- በወለል ደረጃዎች መካከል የሚደረጉ መሸጋገሪያዎች ከ ½" በታች የሆነ የተስተካከለ ጠርዝ ወይም ከፊፍ የሌላቸው ከሆነ።

*በዚህ ሰነድ ውስጥ የተካተተው መረጃ የህግ ምክር ስላይደለ እንደዛ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። የህግ የምክር አገልግሎት ለማግኘት፣ እባክዎትን ጠበቃ ያነጋግሩ።*